ከጌትነት ኖርዌ

እውነትም የብልሆች አምባ!!

# አሲምባ

እንዴት ነሽ አሲምባ
የብልሆቹ አምባ

ማአሴ ነጋ አሲምባ
አልጌዎናዬ በይኘ እባ

ከላሳ ስንገደ አሊተና ዳያ
ቆሎመሽላ እስላም ተወዲያ

ኢሮብ ቤዝአምባችን
መኩሪያ ከለላችን
የልጅነት ዝናር መንጎማለያችን
የትግል ትምህርትቤታችን
የጓዳዊ ፍቅር መሠረት ቤታችን

አላወላውልም ፍጹም ነው እምነቴ
የጠላቱ ሳንጃ ቢደቀን ከፊቴ

ብለን የዘመርንብሽ
አለኘታነታችንን ያሳየንብሽ
ምስዋዕትነትን የደፈርንብሽ

በሶስትጥምር ጠላት ከበባ በጽኑ የተጎዳንብሽ
አሲምባችን እንዴት ነሽ

የእነደብተራው ልጆች አሁንም
በጽናት ቆመናል አናወላውልም

ለጓድ ሞት አያለቅሱምና
የጓድ አጽም እሾክ ሆኖ ይውጋና!!